# በቆሼ መነጽር

ስሜነህ 03-27-17

ባሳለፍነው ክረምት ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ ሲዋዥቅ የነበረው ዝናብ በከተሞቻችን የጎርፍና የአተት ስጋቶችን ጥሎብን የከፋም ባይሆን ዋጋ አስከፍሎን ማከፉ አይዘነጋም። በኤሊኖ ክስተት ሲጠበቅ የነበረው ከባድ ዝናብ ከድርቁ ለማገገም ቢረዳንም ባስከተለው ከፍተኛ ጎርፍ ከኢትዮጵያ ሶማሌ ጅግጅጋ ጀምሮ በድሬደዋ፤ ኦሮሚያ/ምእራብ አርሲና በደቡብ የአላባ ልዩ ወረዳ፤ እንዲሁም በስልጤ ዞን ሳንኩራ ወረዳ ላይ አስከትሎ የነበረው የሰው ህይወትንም የጨመረ ጥፋት የማይረሳ ነው። ይህ ክስተት በከተሞች የበረታው ካለን ደካማ የፍሳሽ ማስወገጃ ስርአት ጋር ተያይዞ መሆኑም አያከራክርም።

ለተላላፊ በሽታዎች መዛመት ቅርብ የሆኑት የጋራ መኖሪያ መንደሮችን ጨምሮ በአራቱም ማዕዘናት የሚገኙ መንደሮች በቆሻሻ መዋጣቸው እንዲህ አይነት አጋጣሚዎችን ለመቋቋም አዳጋች አድርጎት የነበረ መሆኑም አይዘነጋም፡፡ ለበርካታ ቀናት በዋና መንገዶች ላይ ሳይቀር ተከምሮ የነበረው ቆሻሻ ነዋሪዎችን ምን ጉድ መጣ አሰኝቶ ያለፈ መሆኑም በተመሳሳይ፡፡ ነገሩን አሳሳቢ አድርገውት ከነበሩት ጉዳዮች መካከል ለዓይንና ለአፍንጫ ከባድ ለነበረው የቆሻሻ ቁልል መፍትሔ የሚፈልግለት አካል ጠፍቶ የነበረ መሆኑና፤ ለተፈጠረው ችግር መፍትሔው ምን እንደሆነ በድፍረት ወጥቶ የሚናገር አለመገኘቱ መሆኑም አይረሳም፡፡

*አዲስ አበባ የፌዴራል መንግሥቱን ጨምሮ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ እንደመሆንዋ መጠን፣ ለከተማዋ የሚያስፈልጉ መሠረተ ልማቶችን የማሟላት ሃላፊነት የማን ነው? በውኃ፣ በቆሻሻ አወጋገድም ሆነ በሌሎች ጉዳዮች ትልቂቱ አዲስ አበባችን ምን መምሰል እንደሚኖርባት ማሰላትና ማሰብ ያለበትስ ማነው? በእርግጥም መንደሮቻችን ከዳር እስከ ዳር በቆሻሻ ሲዋጡ መመልከት የመዘጋጃ ቤቶቻችን ስራቸው ምንድን ሆነና ነው? ያሰኛል። በመለወጥ ላይ ያለው የአገሪቱ ገጽታ ወደኋላ ቢመለስ ተጠያቂዎቹ እነማን ሊሆኑ ነው?።* ብለን ባሳለፍነው ክረምት ያነሳነው ጥያቄ መልስ ሳያገኝ ሌላና የመዘጋጃ ቤቶቻችንን የሃላፊነት ደረጃ ጥያቄ ላይ የሚጥል አደጋ በቆሼ ገጠመን።

አዲስ አበባ ከተማ የአገሪቱ ርዕሰ መዲና መሆኗን ተከትሎ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ የሚኖርባት ብቻ ሳትሆን በአራቱም አቅጣጫ ህዝብ እየጎረፈባት ያለች ከተማ ናት። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የነዋሪዎቿ የፍጆታ መጠን ከፍተኛ መሆኑ የማያጠያይቅ ሲሆን በዚያው ልክ የሚወገዱ ተረፈ ምርቶችም ከፍተኛ መሆናቸው እና ከለት እለትም እየጨመረ የሚሄድ መሆኑም አያከራክርም። ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ከክረምቱ ጎርፍ ጋር ብቻ ተያይዞ ሳይሆን፣ በከተማው ነዋሪ ማደግ ልክ የሚያስወግደው ተረፈ ምርት በዚያው ልክ ማደጉን ያላገናዘበው ደካማ የቆሻሻ አወጋገድ ስርዓታችን በቆሼ ተገልጦ የችግሩን ስፋትና ጥልቀት በሚገባ ሊያሳየን በቅቷል።

የአዲስ አበባን ቆሻሻ በሰንዳፋ ከተማ እንዲጣልና በምትኩም ቆሻሻው በፋብሪካ መልክ ተቀይሮ ለአገልግሎት እንዲውል ከፈረንሳይ መንግስት በተገኘ ድጋፍ ወደ ስራ የተገባ ቢሆንም እስካሁን ተግባራዊ መሆን ያልቻለበት ምክንያት አለመታወቁ እና ለህዝብ አለመገለጡ በእርግጥም ግና በስጋት ውስጥ ስለመሆናችን ያመላክታል። እንደዚህ አይነት እንዝህላልነት ያለባቸው የአፈጻጸም ስህተቶች ለሰው ህይወት መጥፋት ምክንያት ሲሆኑ መመልከት የአደጋውን አስከፊነትና የወደፊት ስጋት ያጠይቃል። ከዚሁ የቆሻሻ ናዳ መደርመስ በዘለለ ደግሞ ወደፊትም ሆነ አሁንም ለአዲስ አበባ ነዋሪዎች ፈታኝ የሆነው የአካባቢ ንጽህና ጉድለት ነው። ከተማዋ የሚፈለገውን ያህል የህዝብ መጸዳጃ ቤት የላትም። የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቱቦዎችም ቢሆኑ አስተማማኝ ባለመሆናቸው ወደ ፊት ከአሁኑ የባሰ አደጋ ሊከሰት ስላለመቻሉ ዋስትና የለንም።

እንዲህ አይነቱ አሳዛኝ አደጋ በአገር ላይ ሲደርስ አገርንና ሕዝብን ከሰው ሠራሽና ከተፈጥሮ አደጋዎች ከመከላከል አንጻር ብቻ ሳይሆን የአህጉሪቱ ከተማ ከመሆኗም አንጻር ጉዳዩን ተመልክቶ መነጋገር ተገቢ ነው፡፡ የአገሪቱን ዜጎች ከአደጋ ሥጋት መጠበቅ የመንግስት የመጀመሪያና መሰረታዊ ስራ ነው፡፡ የአገሪቱ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 14 ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደኅንነትና የነፃነት መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡ ይህ ይደንገግ እንጂ፣ የሰሞኑ አደጋ ሲታይ ከዚህ በተፃራሪ በመሆን እየኖርን ያለን ያስመስላል።

በእርግጥ የኢትዮጵያ መንግስት በቆሻሻ ድርመሳው አደጋ የተሰማውን ሀዘን ገልጾ ተገጂዎች በዘላቂነት የሚደገፉበትን መንገድ እንደሚያመቻች ከመግለጽ ባለፈ በተጠናከረ

ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ስለመገኘቱ በርካታ ማሳያዎችን መጥቀስ ይቻላል። ከገንዘብ ማሰባሰብ ጀምሮ ጊዚያዊ መጠለያዎችን የማቋቋምና ዘላቂ የሆኑ የመኖሪያ ስፍራዎችን በማመቻቸት ላይ ነው። ያም ሆኖ አሁንም በአደጋ ቀጠና ውስጥ የሚገኙ መንደሮች በርካታ መሆናቸውን ከዚሁ ዘመቻ ጋር አያይዞ ማጤንና መላ የመሻቱ ጉዳይ ስለመዘንጋቱ አመላካች የሆኑና ከስጋት ጋር ስለመሆናችን የሚያጠይቁ በርካታ ማሳያዎች አሉ።

ከፍተኛ ሀብት ፈሰባቸው የተገነቡ መንገዶች በዘፈቀደ ሲቆፋፈሩና ሲፈራርሱ ይታያሉ፡፡ የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች በአግባቡ ስላልተገነቡ ጠብ ባለ ቁጥር በመንገዶቹ ላይ ወራጅ ውኃ እንዲጋለበባቸው ነው፡፡ ክረምት እየተጠበቀ በግንባታ ሰበብ በየቦታው በተገነቡ መንገዶች ላይ ሳይቀር ቁፋሮ መካሄዱም ሁነኛ ማሳያ ነው፡፡ አምና ሬንጅ ለብሰው የነበሩ መንገዶች ዛሬም ፈርሰው የለበጣ ግንባታ እየተከናወነባቸው መሆኑም በተጨባጭ የሚታይ የድክመታችን ማሳያ ነው፡፡

ይህ አደጋ የደረሰበት የቆሻሻ ማስወገጃ ሥፍራ (ቆሼ) በአንድ ወቅት ተዘግቶ ነበር፡፡ የቆሻሻው ክምር መጠን ከ300 ሜትር በላይ በመግዘፉ የተነሳም በተለያዩ ጊዜያት በአካባቢው መንሸራተት ማጋጠሙን የሚያውቀው አስተዳደር ስለምን በዝምታ እንደቆየ እና ወደአዲስ ቆሻሻን መልሶ የሃይል ምንጭ የማድረግ ፕሮጀክት ሲሸጋገር ጉዳዩን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ስርአት አለመዘርጋቱ የሚያጠያይቅ ነው፡፡

አደጋን አስቀድሞ መከላከል መቻል የሰው ልጆችን ሕይወት ከመታደግ በተጨማሪ፣ ለሌላ ጊዜም አሥጊ እንዳይሆን የራሱን ሚና ይጫወታል፡፡ የአስተዳደሩን ምን ላይ መሆን የሚያጠይቀው ጉዳይ አደጋው በራሱ ለብቻው አይደለም። ከአደጋው በኋላ የተመለከትነው የአደጋ መከላከል አቅማችን እና ስርአታችንም ጭምር ነው። አደጋው በደረሰበት ሥፍራ በቂ የቁፋሮ ማሽኖችንና የአደጋ ጊዜ ሠራተኞችን በማሰማራት በቅልጥፍና መሥራት ባለመቻሉ፣ የአካባቢው ሰዎች በዶማና በአካፋ ቁፋሮ ላይ ተሰማርተው ታይተዋል፡፡ ከቅድመ መከላከል እስከ አደጋው ማግሥት ያለው ሒደት የአቅም አለመገንባትን ያሳያል፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ልብ የሚነካ የቤተሰቦች ሐዘንና ግራ መጋባት ችግሮችን በጥልቀት ለመፈተሽ እና ወደፊትን እንድናሰላ ያስችለናል፡፡ ይህ ሥፍራ ባለፉት አሥር ዓመታት

ውስጥ እንደ ሥጋት ይታይ እንደበር በአካባቢው ለረጅም ጊዜ የኖሩ ሰዎች ሳይሆኑ መንግስትም ሲናገረው የነበረ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በንግግር ሳያበቃም ቆሻሻ ከመጠን በላይ የተከመረበት ይህ የቆሼ ተራራ በተደጋጋሚ መንሸራተቱንም ነዋሪውም ሆነ አስተዳደሩ አሳምሮ ያውቀዋል፡፡ ታዲያ ግዴለሽነትን ምን አመጣው? በቀን ከ500 በላይ ሰዎች የሚውሉበት የቆሻሻ ማስወገጃ ሥፍራ በግምት በከተማው በዓመት ከሚሰበሰበው 300 ሺሕ ቶን ቆሻሻ አብዛኛው እንደሚከማችበት ይታወቃል፡፡ ይህ ሥፍራ ለራሱ ብቻ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት አያስፈልገውም? ይህንን ተግባር መፈጸም ያለበት ባለቤት የለውም? ይህ የአደጋው ሰለባ የሆኑ ዜጎችን ከማቋቋም ጎን ለጎን ምላሽ የሚያሻው ጥያቄና  ተጠያቂው አካል ተለይቶ እንዲጠየቅ የማድረግ የአስተዳደሩ ስራ ሊሆን ይገባል፡፡

ችግሩ የባለሙያና የተቋም ሳይሆን የግዴለሽነት መሆኑን የሚያመላክተው አደጋው እየቀረበ መምጣቱን አሳይተው የነበሩ ከላይ የተመለከቱ የመንሸራተት ፍንጮችን ታሳቢ ያደረገ አንዳች ስራ አለመሰራቱ ነው፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የተለያዩ አደጋዎች ሲደርሱ ክሬኖችና የመቆፈሪያ ማሽኖች ስለማይገኙ በውሰት ከሌላ ቦታ እስኪመጡ ከባድ የሚባሉ አደጋዎች መድረሳቸው እና አሁንም በአደጋ ቀጠና ላይ የተንጠለጠሉ በርካታ መንደሮች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ ስለሆነም በቆሼ አደጋ ማዘንና የአደጋውን ሰለባዎች ከማቋቋም ባሻገር የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት አቅምን በመገንባት ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችን ለመቀልበስ የሚያስችል ሥርዓት መገንባት ያስፈልጋል፡፡

በከተማው መንገዶች ላይ ተገቢውን ቁጥጥርና የመከላከል ሥራ ከማከናወን ባሻገር በየገደላ ገደሉ ላይ ለተንጠለጠሉ መንደሮችም መላ መሻት ያስፈልጋል። በመንገዶችና በግንባታ ሥፍራዎች ተከፍተው የተተው ጉድጓዶች ሊደፈኑ ይገባል። ሕግ ባለመከበሩ ብቻ የተዝረከረኩ አሠራሮች በዝተዋል፡፡ በመሠረቱ በእንዲህ ዓይነት አካባቢ ሰዎች መኖሪያቸውን መሥርተው ሊኖሩ አይገባም፡፡ የከተማ አስተዳደሩ ሚቴን የተባለ በካይ ጋዝ የሚያመነጭ አካባቢ ውስጥ የዕለት እንጀራቸውን ከመፈለግ ጀምሮ መኖሪያቸውን ሲመሠርቱ ዝም ማለት አልነበረበትም፡፡ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ 513/1999 መሠረት የአካባቢ ጥበቃ ደረጃን በመከተል የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ መገንባት፣ የአካባቢ ኦዲት

መካሄዱን ማረጋገጥ፣ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረትም የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ መካሄዱን ማረጋገጥ ግዴታ ነው፡፡ ይህም ግዴታ በከተማ አስተዳደሮች ላይ ተጥሏል፡፡ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ በሥራ ላይ እያለ ወይም ከተዘጋ በኋላ በአካባቢ፣ በሰው ጤና ወይም በንብረት ላይ ጉዳት ካደረሰ ጥፋተኝነትን ማረጋገጥ ሳያስፈልግ ባለቤቱ ኃላፊ ይሆናል ሲልም ደንግጓል፡፡ ይህ ተከብሯል? የአደጋው ሰለባ የሆኑ ዜጎችን ከማቋቋም እኩል በኩል መልስ ሊሰጠው የሚገባው እና ህዝብ የሚጠብቀው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ዘመን ቆሻሻ ከፍተኛ ጥቅም ያለው ሀብት ነው፡፡ ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ያገለግላል፡፡ ሃገራችንም ቆሻሻን ወደ ኢንቨስትመንት ለመቀየር እየተጋች መሆኑ ተገቢ ቢሆንም ሂደቱ የአደጋን ስጋትና የመከላከል አቅምን ታሳቢ ያደረገ ሊሆን ይገባዋል።